| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ጽሑፍ ፤ "ዜና ፡ ስሌት ። " |
| ርእስ ፤ | "ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፤<br>የተሟላ ፡ ያማርኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ማረሚያ ። " |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ። |
| ዕለት ፤ | ግንቦት ፡ 2011 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቍ.2011-002 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ዜና ፡ ስሌት ።

Computing News | Nouvelles d'informatique

## ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፤

## የተሟላ ፡ ያማርኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ማረሚያ ።

—

ዐውደ ፡ ቀለም ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ የመዠመሪያው ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ነጻ ፡ ባለፊደል ፡ መጠ̊ንቀቂያና ፡ ባለመዝገበ ፡ ቃላት ፡ የጽሑፍ ፡ ማምረቻ ፡ መግበር ፡ ነው ። የመዠመሪያ ፡ ክለሳው ፡ መስከረም ፡ 16 ፡ ቀን ፡ 2008 ፡ ዓ.ም. ፥ ክለሳ ፡ 1.2 ፡ ደግሞ ፡ ሚያዝያ ፡ 30 ፡ ቀን ፡ 2011 ፡ ወጥቷል ።

ያማርኛ ፡ ቋንቋ ፡ ቃላትን ፡ የማርባት ፣ የመዘርዘርና ፡ የማዋሐድ ፡ ጠባይ ፡ ስላለው ፥ ርሱን ፡ የሚመጥን ፡ የፊደል ፡ መጠ̊ንቀቂያ ፡ ለመሥራት ፡ እጅግ ፡ ያስቸግራል ። ለማስታወሻ ፡ ያኽል ፡ የሚከተለውን ፡ እንመልከት ።

በእንግሊዝኛ ፡ *"we dream the world"* ፡ ቢል ፥ ወይ ፡ በፈረንሳይኛ ፡ *"nous rêvons le monde"* ፡ ቢል ፥ ወዳማርኛ ፡ ስንተረጕመው ፥ "ዓለምን ፡ ዐለምን" ፡ ይላል ። ነገር ፡ ግን ፥ ሳንጠነቀቅ ፥ ዐማርኛውን ፡ በሌላ ፡ ዐይነት ፡ የጻፍነው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ወይ ፡ ስሕተት ፡ ይኾናል ፥ አለዚያም ፡ ትርጕምን ፡ ይለውጣል ። ለምሳሌ ፦

"አለምን ፡ ዐለምን" ፡ ቢል ፥ "ምንም ፡ ሳይኖረን ፡ ሕልምን ፡ ዐለምን" ፡ ማለት ፡ ይኾናል ።

"አለምን ፡ ዓለምን" ፡ ቢል ፡ ደግሞ ፥ "ዓለምን ፡ አስለምን" ፡ ማለት ፡ ይኾናል ።

"አለምን ፡ አለምን" ፡ ቢል ፡ ደግሞ ፥ "ምንም ፡ ምን ፡ ሳይኖር" ፡ ማለት ፡ ይኾናል ።

"አለምን ፨ አለምን ፨ " ፡ ቢል ፡ ደግሞ ፥ "ብሷልምን ፨ ብሷልምን ፨ " ማለት ፡ ይኾናል ።

ወዘተ... ።

እንዲህ ፡ የተወሳሰበውን ፡ ያማርኛ ፡ አጻጻፍ ፡ ነው ፡ "ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ የቃኘልን ።




ከዚህ ፡ ወዲያ ፥ ቃላትን ፡ በሦስት ፡ ቋንቋዎች ፡ ባማርኛ ፣ በእንግሊዝኛና ፡ በፈረንሳይኛ ፥ ርስ ፡ በርሳቸው ፡ ያተራጕማል ። ክለሳ ፡ 1.2 ፡ ደግሞ ፡ ግእዝንና ፡ ሶማልኛን ፡ በጥቂቱ ፡ ማተራጐም ፡ ዠምሯል ።

በዚያው ፡ በ"ዐውደ ፡ ቀለም" ፡ መሳሊያ ፡ ውስጥ ፦

- ያማርኛ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ (የደስታ ፡ ተክለ ፡ ወልድና ፡ የተሰማ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል) ፤
- የግእዝ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ (የኪዳነ ፡ ወልድ ፡ ክፍሌ) ፤
- የእንግሊዝና ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ (የ WordNet ፡ አሜሪካዊ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት) ፤
- የፈረንሳይኛ ፡ ግስ ፤

ተከተውበታል ።

ያሜሪካን ፡ እንግሊዝኛ ፡ ጽሑፍንና ፡ የሶማልኛን ፡ የቁቤ ፡ ጽሑፍ ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵኛ ፡ ጽሑፍ ፡ ለመመለስ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

የሚያስችል ፡ መመለሻም ፡ ዐብሮ ፡ ተሰጥቷል ።  ይህ ፡ በተለይ ፡ ለደራስያንና ፡ ለማወራኛ ፡ ድርጅቶች ፡ እጅግ ፡ የሚረዳ ፡ አገልግሎትን ፡ ይሰጣል ።

ሙሉ ፡ መረጃውን ፡ ዐብሮት ፡ ከሚመጣው ፡ የ 107 ፡ ገጽ ፡ መመሪያ ፡ ማግኘት ፡ ይቻላል ።

*"ዐውደ ፡ ቀለም"* ፡ ነጻ ፡ መሳሊያ ፡ ነው ፤ ከመርበቢያው ፡ ከ awdeqelem.net ፡ በነጻ ፡ ይገኛል ። ዐብሮት ፡ *"ዋዜማ ፡ ሥርዐት* 🇪🇹 *"* ፡ የተባለ ፡ የመፍቻ ፡ ገበታና ፡ የቅርጸቶች ፡ ሥርዐት ፡ ይመጣልና ፥  ማንኛውም ፡ ሰው ፡ ወዲያውኑ ፡ የጽሑፍ ፡ አምራች ፡ ይኾንበታል ።

*"ሥልጡንሕዝብና"* ፡ መዜንውም ፡ በ *"ዐውደ ፡ ቀለም"* ፡ ስለሚሠራ ፥  ጥቅሙን ፡ በገቢር ፡ አግኝቶበታል ❖


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።